| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ዜና ፡ ስሌት ።" |
| ርእስ ፤ | "5G ፡ ወይም ፡ 5 ኛ ፡ ትውልድ ፡ እና ፡ እኹል-ገብ ፡ ኢንተርኔት ።" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ዜና ፡ ስሌት ።

Computing News | Nouvelles d'informatique | اخبار العقل

## 5G ፡ ወይም ፡ 5 ኛ ፡ ትውልድ ፡ እና ፡ እኹል-ገብ ፡ ኢንተርኔት ።

—

**የአንከርት ፡ ስልክ ፡ ኪነት** ፡ (mobile phone technology) ፡ በሠላሳ ፡ ዓመታት ፡ ታሪኩ ፥ ዘንድሮ ፡ 5 ኛ ፡ ትውልዱን ፡ ወልዷል ። ወላጅ ፡ ከልጆቹ ፡ የሚለየውን ፡ ያኽል ፡ ይህ ፡ 5 ኛው ፡ የኪነት ፡ ትውልድ ፡ ከቀደሙት ፡ 4G ፡ እና ፡ 3G ፡ ... ፡ ይለያል ።

5G ፡ ከሚያመጣቸው ፡ መሻሻሎች ፡ ውስጥ ፡—

- ፍጥነት ፤ ሽቦ-አልቦ ፡ (wireless) ፡ የሚተላለፈው ፡ የስልክ ፡ መልክት ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ 20 ፡ Gbps ፡ (Giga bits per second ፥ ወይም ፡ 20 ፡ ቢልዮን ፡ ኹለትዮ ፡ ንምራ ፡ በካልኢት) ፡ ይደርሳል ፡ (በ 4G ፡ ከ 1Gbps ፡ አያልፍም) ።

- የሥርጭት ፡ ዝግየታው ፡ (latency ው) ፡ ካ 1 ፡ ms ፡ (milliseconds ፡ ወይም ፡ ካ 1 ፡ ካልኢት-ሺኛ) ፡ አይበልጥም ።

- የበለጠ ፡ ፈሰሳ ፡ (bandwidth) ፡ እና ፡ የተሻሻለ ፡ የቀጠጥና ፡ ኪነት ፡ (antenna technology) ፡ ስለሚኖር ፥ በ 5G ፡ የሚዘዋወረው ፡ ልቅም ፡ (data) ፡ መጠን ፡ የላቀ ፡ ይኾናል ።

- 5G ፡ የቀለጠፈ ፡ የመርበብት ፡ አስተዳደር ፡ (network management) ፡ ስለሚኖረውም ፥ ከእውነተኛው ፡ 5G ፡ መርበብት ፡ ጋራ ፡ ሌሎች ፡ የመርበብት ፡ ክፍለቶችን ፡ ለመፍጠርና ፥ ለእያንዳንዱ ፡ የተለየ ፡ አስተዳደር ፡ ለመመደብ ፡ ያስችላል ።

ሽቦ-አልቦ ፡ መርበብት ፡ የሚዘረጋው ፡ በማቄሪያ ፡ (cell) ፡ ማማ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ሥርጭቱ ፡ ከማቄሪያ ፡ እማቄሪያ ፡ በሚቀባበል ፡ የምዕዛር ፡ (radio) ፡ ሞገድ ፡ (wave) ፡ ይከናወናል ። ኾኖም ፥ ለ 4G ፡ ረኻፉም ፡ የማቄሪያ ፡ ማማ ፡ ሩቅ ፡ ለሩቅ ፡ ያስፈለገውን ፡ ያኽል ፥ ለ 5G ፡ ደግሞ ፡ ቅርብ ፡ ለቅርብ ፡ የተተከሉ ፡ አነስተኛዎች ፡ ማማዎች ፡ ይበቁታል ፥ ምክንያቱም ፥ እጅግ ፡ ፈጣን ፡ ሥርጭት ፡ እንዲኖረው ፡ ብዙ ፡ ርቀት ፡ በማይዘልቅ ፡ በከፍተኛ ፡ የምዕዛር ፡ ብዛት ፡ (frequency) ፡ ይሠራል ። ይህ ፡ ኹኔታ ፡ ግን ፡ 5G ን ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የአካልና ፡ የአየር ፡ ጠባይ ፡ መሰናክሎች ፡ ይዳርገዋል ።

ባኹኑ ፡ ሰዓት ፥ 5G ፡ ዐሥር ፡ እማይሞሉ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ባነስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተዘርግቷል ፤ በመላ ፡ ዓለም ፡ እስኪዘረጋ ፡ 10 ፡ ዓመት ፡ ይፈጃል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

5G ፥ በማሠራጫ ፡ ፈጣንነቱ ፣ በፈሰሳ ፡ ብልጫውና ፡ በመለስተኛ ፡ ዝግየታው ፡ ላዳዲስ ፡ ኪነቶች ፡ አዋዋል ፡ ይመቻል ። ከነዚህ ፡ ዐዳዲስ ፡ ኪነቶች ፡ ውስጥ ፥ ነጂ-አልቦ ፡ መኳኳኘ ፣ በ"ሮቦት" ፡ የታገዘ ፡ የርቀት ፡ ሥራ ፡ ይገኙበታል ።

በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ባኹኑ ፡ ሰዓት ፡ እጅግ ፡ ለሚስፋፋው ፡ *"እኹል-ገብ ፡ መርበብት"* ፡ ወይም ፡ *"Internet of Things"* ፡ በር ፡ ይከፍትለታል ። እንደ ፡ ልብስ ፡ ማጠቢያ ፣ ማቀዝቀዣ ፣ መኪና ፣ ስልክ ፣ የቤት ፡ ማሞቂያ ፣ ... ፡ ያሉ ፡ መሣሪያዎች ፥ እንደ ፡ ሰዉ ፡ ኹሉ ፥ የ IP ([1]) ፡ አድራሻ ፡ ኖሯቸው ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ኾነ ፡ ካንዳች ፡ ማእከል ፡ ጋራ ፡ በ 5G ፡ መርበብት ፡ አማካይነት ፥ *"ደከመኝ ፤ ሰለቸኝ"* ፡ ሳይሉ ፥ መረጃን ፡ በማቀበል ፣ መቀባበልና ፡ ማቀባበል ፡ አካባቢውን ፥ ለደኅናም ፡ ኾነ ፡ ለሌላ ፥ መቈጣጠርን ፡ ያስችላሉ ።

እውነት ፡ ለመናገር ፥ 5G ፡ የሚያስችለው ፡

---

1 IP ፡ ወይም ፡ Internet Protocol ፤ ከምንጩ ፡ እስከ ፡ መድረሻው ፡ የመረጃን ፡ የኢንተርኔት ፡ ፍናዌ ፡ ወይም ፡ አላላክ ፡ ዝርዝር ፡ የሚቈጣጠር ፡ ሥርዐት ።


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ነገር ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ተዘርዝሮ ፡ የሚታወቅ ፡ አይደለም ። ገና ፡ ማንም ፡ ዛሬ ፡ ያላሰባቸው ፡ ብዙ ፡ አዋዋሎች ፡ ስለሚኖሩት ፥ በተለይ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ለየብቻቸው ፡ ጠቅልሎ ፡ የመያዝ ፡ ፍላጎትን ፡ ካኹኑ ፡ ማሳየት ፡ ዠምረዋል ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ካልተጠነቀቀ ፥ ምናልባት ፡ ሳያውቀው ፡ ነጻነቱንም ፡ በመርበብት ፡ ሊነጠቅ ፡ ይችላልና ፥ ዘው ፡ ዘው ፡ ከማለቱ ፡ በፊት ፡ ለነጻነቱ ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ መኖሩን ፡ አስቀድሞ ፡ ማረጋገጥ ፡ ይገባዋል ፨

---

## የ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ መርበቢያ ፡ awdeqelem.net ፡ ከነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ አላግባብ ፡ ታግዷል ።

"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የተባለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ መርበቢያ ፡ awdeqelem.net ፡ ከነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ መታገዱን ፡ ባለቤቱ ፡ አቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፡ ገልጸውልናል ።

የታገደበትን ፡ ምክንያት ፡ ሲያብራሩ ፥ የመርበቢያው ፡ አከራይ ፥ ፈረንሳዊው ፡ ድርጅት ፡ Groupe Magic Online ፡ ባሳየው ፡ ያገልግሎት ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፥ ለሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ደንበኞነታቸውን ፡ እንደማይቀጥሉ ፡ አሳውቀውት ፥ ከሌላ ፡ አከራይ ፡ ጋራ ፡ በሚነጋገሩበት ፡ ወቅት ፥ የኪራዩ ፡ ዘመን ፡ ከማለቁ ፡ 2 ፡ ወራት ፡ በፊት ፥ Groupe Magic Online ፡ (https://magic.fr) ፡ የመጪውን ፡ ዓመት ፡ ኪራይ ፡ አለፈቃዳቸው ፡ ከባንክ ፡ ሒሳባቸው ፡ ወስዶ ፥ ገንዘቡንም ፡ መልስ ፡ እንዳይባል ፥ መርበቢያቸውን ፡ ሳልጠየቁት ፡ ለሌላ ፡ አከራይ ፡ አኹንም ፡ አለፈቃዳቸው ፡ በማዛወሩ ፡ በተፈጠረ ፡ ውዝግብ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

አኹን ፥ ጕዳዩ ፡ የመርበቢያዎችን ፡ ስም ፡ ምዝገባና ፡ ጠቅላላ ፡ ጕዳይ ፡ በበላይነት ፡ ለሚመለከተው ፡ ለ ICANN ፡ ስለ ፡ ቀረበ ፥ ከምርመራ ፡ በኋላ ፡ የሚሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ እንደሚጠባበቁ ፡ ገልጸውልናል ።

Groupe Magic Online ፡ የተባለው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ድርጅት ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ.ንም ፡ መርበቢያ ፡ (slttunhzb.net) ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ ማወኩ ፡ ይታወሳል ። ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጕዳዩን ፡ ለፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ምጋቤ ፡ ካቀረበው ፡ በኋላ ፥ መርበቢያውን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አከራይ ፡ ድርጅት ፡ ማዛወሩ ፡ ይታወሳል ።

"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የተባለውን ፡ መግበር ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ስለሚሠራበትና ፡ ያገልግሎቱንም ፡ ጥቅም ፡ ለሌሎች ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ስለ ፡ ወደደ ፥ በባለቤቱ ፡ በአቶ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፡ ፈቃድ ፥ መግበሩን ፡ ማንኛው ፡ ሰው ፡ ከመርበቢያችን ፡ ከ slttunhzb.net ፡ በነጻ ፡ ሊቀዳው ፡ እንደሚችል ፡ እናስታውቃለን ።

የጕዳዩን ፡ አካኼድ ፡ ተከታትለን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዘግባለን ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።